## ኅብረ-ብሔራዊው ኢ.ሕ.አ.ፓ. ዛሬም የትግራይም ጭምር ነው!

## ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተሰጠ መግለጫ

**መስከረም 20/2017 ዓ/ም**

የጥንታዊትዋ ኢትዮጵያ ዕውቅ ታሪካዊ ማዕከሎች ውስጥ ቀደምቶች የሆኑት አክሱምና ይሃ የሚገኙት በዛሬይቱ የትግራይ ክልል ዉስጥ ነው። የመላ ኢትዮጵያ፣ የመላው አፍሪካና የሁሉም ጥቁር ህዝብ መኩሪያ የሆነው የአድዋ ድል የተመዘገበው በዚሁ ክልል፣ በአድዋ ተራሮችና ሸንተረሮች ነው። እንደ አሉላ አባነጋ ያሉትን ስመ-ጥር ጀግኖቻችን ያፈራችው ትግራይ ናት። ታዲያ ፣ በኢትዮጵያ ረዥም ታሪክ ዉስጥ የትግራይ አስተዋጽዖና ተሳትፎ በዚህ አልቆመም።

ወትሮ ኢትዮጵያውያን በመጡበት አካባቢ እንጂ በዘር አይታወቁም ነበር። በርካቶች እስከመጨረሻው በዘር ሳይተዋወቁ ነው ሙሉ ዕድሜያቸውን አሳልፈው በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት ያሸለቡት። ኢሕአፓና ያ ትውልድ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ላይ ወርድና ቁመት በመጨመር አፍሪካዊነትን፣ የጥቁር ሕዝብ ክፋይ መሆናችንን፣ ዐለም-ዐቀፋዊነትን፣ ሰብዓዊነትን ደርበው አድምቀውታል። ጠባብ-ብሔረተኝነትን አንዴም በውስጣቸው ሥፍራ አልሰጡትም። እንደ ፖለቲካ ችግር ከማየታቸው በስተቀር። እንዴት ተብሎ?! የኢሕ አፓ መሥራች አባላት፣ የተሰባሰቡት ያለጥርጥር በኢትዮጵያዊነት ድርጅታዊ ማዕቀፍ ቢሆንም ምልከታቸው ከዚያም የሠፋ ነበር።በወቅቱ ከፊል አፍሪካን በጭቆና እና ብዝበዛ ያሰቃይ የነበረውን ዘረኝነት ትውልዱ እጅግ ይጠላው ስልነበር ወደ ዚምባብዌ ዘምተን "ኢያን ስሚዝ የሚባል ግለሰብ በእንግሊዝ ታግዞ ያወጀውን የነጭ-ዘረኛ አገዛዝ ተዋግተን እንገርስስ" ብሎ የጠየቀ ትውልድ አካል ነው" ኢሕ አፓ!! ኢሕ አፓ ደግሞ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ወገኑ፣ መላውን ኢትዮጵያም ሀገሩ አድርጎ ነው የተደራጀው፣ የታገለውም። ኅብረ-ብሔራዊነት፣ ኢትዮጵያዊነት፣ አገራዊነት፣ አፍሪካዊነት፣ ... የኢሕ አፓ አባላት የሚኮሩባቸው ማንነቶቻቸው ነበሩ።

ይህንኑ ኢሕአፓዊ ማንነት በግንባር አጉልተው ያራምዱ የነበሩ አባላቱ ከታሪካዊትዋ ትግራይ ክልልም ጭምር የመነጩ ነበሩ። ከታወቁት የተወሰኑትን ለመጥቀስ እንሞክር። በርካታ የትግራይ ነዋሪ በዝነኛው

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴና ትግል ዉስጥ፣ በኋላም በኢሕአፓና በ ኢሕአሠ ውስጥ ትልቅ አበርክቶት ነበራቸው። መስፍን ሃብቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ምሥረታ እስከ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጎ ኒውዮርክ ዉስጥ በአልታወቁ ሃሎይች በሴጋነት ህይወቱን አጥቷል። ብርሃነ መስቀል ረዳ ከተማሪ እንቅስቃሴ እስከ ኢሕአፓ እና ኢሕአሠ ምሥረታ ትልቅ የመሪነት ሚና የተጫወተ ከፍተኛ ዋጋም የከፈለ ጓድ ነበር። ዮሴፍ አዳነ ከተማሪ እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከ ኢሕአፓ ምሥረታ ትልቅ ሚና የተጫወተ ጓዳችን ነበር። ዮሴፍ አዳነ በደርግ ሰቆቃ ህይወቱ ባለፈበት ወቅት የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር። ፀሎተ ሕዝቅያስ ሌላ ትልቅ ሚና የነበረው በኋላ አሲምባ ኢሕአሠን ተቀላቅሎ የነበረ በወቅቱ የአመራር አባል የነበረ ጓድ ነበር። በአንድ መጥፎ አጋጣሚ ህይወቱን እዚያው ሜዳ ዉስጥ ነው ያጣው። ጓድ ዘሩ ክህሸን ከተማሪ እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከ ኢሕአፓ ምሥረታ ጥሩ የትግል ሚና የነበረው በኋላም የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴ አባል የነበረ ጓድ ነው። ብንያም አዳነ አልጄሪያ ውስጥ ከነበሩት ወጣት አብዮተኞች አንዱ የነበረና በኋላም ከኢሕአፓ መሥራች አባላት አንዱ የነበረ ጓድ ነበር። ብንያም ከኢሕአሠ መሥራች አባላት አንዱ የነበረና የጤና ችግሩን ተቋቁሞ ከጀማሪው ቡድን ጋር ሲጓዝ በጉዞ ላይ እንዳሉ ህይወቱን በማጣቱ የኢሕአሠ የመጀመሪያ መሥዋዕት ከሆኑት ሁለት ጓዶች አንዱ ነበር። መሓሪ ረዳ (ጸሓዬ፣ በህይወት ያለ)፣ የሜዳ ስሙ አሉላ ይባል የነበረው ጽኑ ጓድ፣ ሃዲሽ ዛህላይ፣ ሃዲሽ (ጥቁሩ)፣ ሃይለ ማርያም፣ ዮሀንስ (ሞሼ ዳያን)፣ ጠዐመ፣ ዳዔል (ታዬ፣ በህይወት በውጭ ያለ)፣ ገብረ ጻድቅ (ኅሩይ)፣ ነጋሽ (በርሄ)፣ ሃይሌ ዓባይ (አምባዬ)፣ ተስፋዬ፣ በርሄ (ባለግመሉ)  ካሕሳይ አብርሃ የአሲምባ ፍቅር ደራሲ ፤ በየነ ገብራይ፣ ... ... ስንቱን የትግራይ ጀግናና ጀግኒት እንዘረዝራለን!? በከተማ መዋቅሮች ዉስጥም በርካቶች ይሳተፉ ነበር። በርካቶቹም ከፍተኛ ዋጋን ከፍለዋል።

ዝነኛውን፣ በሳሉን፣ የሌሎች ጓዶችን ሕይወት ለማትረፍ ሲል ራሱን በሞት አደጋ ዉስጥ ያቆየውንና፣ በኋላም ከመማርከና በደርግ እጅ ከመውደቅ ሞቱን የመረጠውን፣ የኢሕአፓ ጀግና መሪ፣ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይን የለገሰችን ትግራይ ናት። ሞት አይፈሬውን፣ ያለጥርጥር ጀግናውን፣ የጽናትና ቁርጠኛነት ምሣሌ የነበረውን፣ ለመስዋዕትነት ሁሌም ራሱን ዝግጁ አድርጎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ "የተሻለ ወደፊትን" ለማምጣት ሲታትር የኖረውን፣ ገብረ እግዚአብሔር ገብረ ሚካኤልን (ጋይምን)፣ ያገኘነውም ከዚያው ከትግራይ እናቶች ማህጸን ነበር። ሌላው በሳልና ጽኑ ታጋይ የነበረውን፣ ጓድ ነጋሽን (ጉግሳን) ያበቀለው ያው የትግራይ ምድር ነው። ስንቱን የትግራይ የኢሕአፓ አባላት የነበሩ ሞት-አይፈሬዎች ቆጥረን እንዘልቀዋለን? ኢሕአፓ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅት ነበር፣ የትግራይ የኢሕ አፓ አባላትም በርካቶች ነበሩ። ዛሬም ያንኑ ኅብረ-

ብሔራዊ ማንነቱን ኢትዮጵያዊ እሴቶቹን ጠብቆ እንደገና እያበበና በመላው ኢትዮጵያ እየተስፋፋም ይገኛል። የኢሕአፓ እንደገና ትግራይ ክልል ዉስጥ መከሰትና እንደ ሕጋዊና በሠላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀስ አገራዊ ፓርቲ ስራውን ለመጀመር መቻል ለመላው ኢትዮጵያዊ እንደ አንድ ትልቅ ተስፋ ሰጭ ርምጃ የሚቆጠር ስለሆነ ሁሉንም ዜጎች የምሥራች እንላለን። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ብቻ ሳትሆን ከታሪክ ማኅደሮቻችን አንድዋና ቀዳሚዋም ስለሆነች፣ ለመላው የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎችም እንኳን ለዚህ አበቃችሁ እንላለን።

ኢሕአፓ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለትግራይ ህዝብ ጭምር፣ ዛሬም ፍቅሩና አክብሮቱን እንደያዘ ነው ያለው። ኢሕ አፓ እንደ እሥስት ቀለሙን በየአካባቢው የሚለውጥ ድርጅት አይደለም። ዛሬም እንደወትሮው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን “የተሻለ ነገን” የማምጥጣት ራዕዩን፣ ዐላማዎቹንና ዕምነቱን አቋሞቹን ጠብቆ ነው የሚንቀሳቀሰው። በእርግጠኝነት የትግል ሥልቱ ሠላማዊ ነው። ለትግራይ ወጣቶችም ኢትዮጵያዊነትን ለማለምለምና የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ህይወት ለማሻሻል፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚናፍቀውን ሠላም  ለማስፈን፣ ኢሕአፓን እንድትቀላቀሉ ጥሪውን ያቀርባል። ኢሕአፓ ለዜጎች መብት መከበር፣ ለእኩልነት፣ ለፍትኅ-ርዕት፣ ለማኅበራዊ ፍትኅ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት በጽናት የሚታገል በጽኑና በሳል አባሉቱ የተገነባ የጀግኖች ድርጅት ነው።

የኢሕ አ ፓ አባላት በክልሉ ዉስጥ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኑነትን ለመፍጠር እየሠሩ ይገኛሉ።

ድል ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ!!

መስከረም 20/2017 ዓ/ም